# ከ13ኛው ሀገር አቀፍ የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት የቀረበ መረጃ

አሁንም ትኩረት

## መግቢያ

ሀገራችን በኤችአይቪ/ኤድስ ዘርፈ ብዙ ምላሽ አመርቂ ውጤት አስመዝግባለች። በዚህም ኤችአይቪ/ኤድስ በተመለከተ የተቀመጠውን የምዕተ አመቱን የልማት ግብ ማሳካት ችላለች።

ሆኖም ግን ስኬቱን በዘላቂነት በማስቀጠል በኩል ተግዳሮቶች እንዳሉ እና በተገኘው ውጤት በመርካት መዘናጋት እየታየ ይገኛል። ይህንን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለምላሹ የላቀ ትኩረት በመሥጠት እንዲቀጥል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የኢፌዲሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የኤችአይ ቪ/ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት የሶስተኛው ስትራቴጂክ እቅድ አፈጻጸምን ለማፋጠን የሚያስችሉ ሁለት ሰነዶች አዘጋጅቷል።

የመጀመሪያው ሠነድ "ኤችአይቪ/ኤድስን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የመጨረሻ ምዕራፍ የሕዝብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ሰነድ ሲሆን ይህ ሠነድ በዋናነት ማኅበረሰቡ ስለ ኤችአይ ቪ/ኤድስ ያለውን አጠቃላይ ግንዛቤ ቀጣይነት ባለው መንገድ በማሳደግ የባህሪ ለውጥ እንዲመጣ፤ ጤናማ የሆነ አኗኗር እንዲፈጠር እና ራሱን ከኤችአይቪ መከላከል የሚያስችሉትን ክህሎቶች እንዲያዳብር ለማድረግ ነው። በተለይም በየደረጃው ያለ አመራር፣ አስፈፃሚ እና የአገልግሎት ሰጪ አካላት ሁሉ ለጉዳዩ የበለጠ ትኩረት በመስጠት፤ እንቅስቃሴ ማድረግ የሚችሉበትን አቅም መፍጠርና በየእርከኑ ዝግጁ ሆነው ወደ ተግባር እንዲገቡ ለማድረግ ነው።

ሁለተኛው ሠነድ ደግሞ"የኤችአይቪ አገልግሎቶችን ማግኘት የሚገባቸው የማህበረሰብ ክፈሎችን ለመድረስ የተዘጋጀ ዘመቻ" ነው። ይህ ሠነድ እ.አ.አ. ከ2015-2020 ሲተገበር የተዘጋጀውን ሶስተኛው ስትራቴጂክ እቅድ (Investment Case Approach) ሊደረስባቸው የተቀመጡ ግቦች አፈጻጸምን ለማፋጠን የተዘጋጀ ነው። የማፋጠኛ ዘመቻው ሰነድ ሁለት ምዕራፎች ሲኖሩት የመጀመሪያው ከነሐሴ ወር 2008 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት ወር 2009 ዓ.ም የሚካሄድ ሲሆን በቀጣዩም በዚህ ወቅት የተገኙትን ስኬቶች በመቀመር በቀጣይነት ሥራዎች የሚከናወኑበት ምዕራፍ ይሆናል።

## የዘመቻው ዋና ዓላማ

ለኤችአይቪ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ትኩረት በሚያደርግ የተቀናጀ ዘመቻ ከ80,000 በላይ ኤችአይቪ በደማቸው ሊገኝባቸው የሚችል ወገኖች የፀረ-ኤድስ ሕክምና የአገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ሲሆን ይህንን ለማሳካትም 2.9 ሚሊዮን የሚሆኑ ለኤችአይቪ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች የኤችአይቪ ምርመራና ምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል።

## ዘመቻው የሚያተኩርባቸው ቦታዎች እና የማኅበረሰብ ክፍሎች

ይህ ዘመቻ በመላው ሀገራችን በተመረጡ 176 ከተሞች እና በተጨማሪም ለዚህ ዘመቻ በተመረጡ ትላልቅ የልማት ተቋማት፣ ማረሚያ ቤቶች እና የስደተኞች ካምፕ በአጠቃላይ 206 የምርመራ ቦታዎች የሚተገበር ሲሆን ከዚህ በታች ያሉት የማኅበረሰብ ክፍሎችን በማህበረሰብ እና በጤና ተቋማት ደረጃ ተደራሽ ለማድረግ የሚተገበር ይሆናል።

### 1. በማህበረሰብ አቀፍ ደረጃ የሚደረሱ

- ሴተኛ አዳሪዎች
- የረጅም ርቀት አሽከርካሪዎች
- ተንቀሳቃሽ ሠራተኞች
- የሕግ ታራሚዎች
- ስደተኞች
- በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ልጆች
- ኤችአይቪ በደማቸው የሚገኝ ወገኖች ቤተሰቦች
- የትዳር አጋሮቻቸውን በሞት ያጡ ወገኖች
- በድጋሚ ያገቡ እና
- ትዳር የፈቱ ናቸው።

### 2. በጤና ተቋማት የሚደረሱ የህብረተሰብ ክፍሎች

- የፀረ-ኤችአይቪ/ኤድስ መድሃኒት ተጠቃሚዎች የትዳር ጓደኞችና ሌሎች የቤተሰብ አባላት
- የትዳር አጋሮቻቸውን በሞት ያጡ
- በድጋሚ ያገቡ
- ትዳር የፈቱ
- ተጋላጭ ህፃናት
- ተኝቶ ታካሚዎች እና ህጻናት

## ለዘመቻው ስኬት በየደረጃው ካሉ አመራር አካላት የሚጠበቁ የመምራት እና የማስተባበር ተግባራት፡-

በየደረጃው ያሉ የአመራር አካላት ለዘመቻው ስኬታማነት የሚረዱ የማስተባበርና የመምራት ስልቶችን መዘርጋት፡ ማጠናከር እና መተግበር ይጠበቅባቸዋል። እነዚህም

### ንቅናቄ መፍጠር

ዘመቻውን በተመለከተ ማኅበረሰቡ ግልፅ መረጃ እንዲኖረው የሚያስችል ጠንካራና ቀጣይነት ያለው የማኅበረሰብ ንቅናቄ እንዲፈጠር ማስተባበር፤

### የቦታና ተጠቃሚዎች ልየታ ማካሄድ

ለዘመቻው በተመረጡት ከተሞች ውስጥ ለስርጭቱ ይበልጥ አጋላጭ የሆኑ ቦታዎችን በመለየት ሂደት ውስጥ ተገቢውን የማስተባበር እና የመምራት ሚና መጫወት፤

### የአገልግሎት ጥራትና ተደራሽነትን ማረጋገጥ

ለዘመቻው የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ያለመቆራረጥ እንዲቀርቡ እና የአገልግሎት ተደራሽነትን እንዲረጋገጥ ተገቢውን የአመራር ሚና መጫወት፤

### የክትትልና ግምገማ ስርዓቱን መምራት

ለዘመቻው ስኬት የሚረዳ የተጠናከረ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት መዘርጋት እና ሂደቱንም መከታተል።